# ዳግም ተገናኘን!

## (የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ምሩቃን)

... "ያሰብኩት ተሳካ ያለምኩት ደረሰ፣
ሃሳቤም ተሟላ መንፈሴም ታደሰ፤..."

ለዛሬዋ ጽሁፌ መግቢያነት የመረጥኳት ግጥም፣ በእውቁ ድምጻዊ በጥላሁን ገሠሠ ከተቀነቀኑት አያሌ የማኅበራዊ ዘርፍ ዘፈኖች አንዱ የሆነው ዘፈን አዝማች ናት(በሃሳባችሁ ዜማውን እያስታወሳችሁ ተከተሉኝ፤ በተለይ ከአጃቢ የሙዚቃ መሳሪያዎች መካከል ጎልታ የምትሰማዋን፣ የአየለ ማሞን የማንዶሊን ዜማ እያዳመጣችሁ)።

... ከዛሬ አንድ ዓመት በፊት "አማኒ ኢብራሂም — 'ያልታወቀው' የጥበብ ሰው" በሚል ርዕስ አንድ መጣጥፍ ቢጤ በኢትዮጵያውያኑ ድረ-ገጾች (በኢትዮ-ሚድያ፣ በኢኤምኤፍ፣ በቋጠሮ፣ በጎልጉል...) ላይ ለንባብ አብቅቼ ነበር።

ጽሑፉ እንደወጣ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፣ ከሰላሣ ዓመታት በላይ የትና እንዴት እንዳለ ያላወኩትን፣ በሙዚቃ ሙያ በእጅጉ የተካነውን፣ ሁሌም ብዙዎች በአርዓያነት የሚጠቅሱትንና የቀድሞ መምህራችን የነበረውን ጋሼ አማኒ ኢብራሂምን በስልክ አገኘሁት። (በዚህ አጋጣሚ ዘርፈ-ብዙ መረጃዎችን ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው በማቀበልና አለኝታ በመሆን ያላሰለሰ አገልግሎት ለሚያበረክቱት ድረ-ገጾቻችን የላቀ ምስጋና ይድርሳቸው!)

...በድምጽ ተገናኝተን ባወጋን በዓመቱም በአካል ለመገናኘት በቃን። ከጋሼ አማኒ ጋር ብቻም ሳይሆን፣ ከሰላሣ ዓመታት በፊት አብረን ከተማርናቸው ጥቂት የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት የቀድሞ ተማሪዎች ጋርም ጭምር!

ይህ እውን ሊሆን የበቃው ደግሞ፣ ጥቂት የቀድሞ የያሬድ ምሩቃን፣ አምና በላስ ቬጋስ ከተማ ተሰባስበን፣ አንድ የመገናኛ ዝግጅት ለማድረግ በመወሰናችን ነበር። በላስ ቬጋስ ከተማ ነዋሪ ከሆኑት አስር ያህል የያሬድ ምሩቃን አምስቱ በቋሚነት ዓመቱን ሙሉ ተንቀሳቅሰን፣ ኦክቶበር 25 እና 26 ቀን 2017 ያገናኘንን ዝገጅት አደረስነው።

መነሻ ዓላማችን፣ የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ምሩቃን ማኅበርን ለሚቋቋም መሰረት መጣል ነበር። ሊቋቋም የታሰበው ማኅበር ዓላማ ብለን ያስቀመጥናቸው ነጥቦችም፣ "...በተማሪነት የህይወት ዘመናችን ያሳለፍናቸውን ትዝታዎች የምናድስበት፣ ከፊሎቻችን በሙያው ዙሪያ በስራ ዘመን በቆየንባቸው ዓመታት ያዳበርናቸውን ጥልቅ የሆኑ የጓደኝነት ፍቅርና ቤተሰባዊ መቀራረብ በተሻለ መልኩ የምናጠናክርበት፣ ለት/ቤቱ የበኩላችንን ድጋፍ የምናደርግበት፣ በሙያው ዙሪያ መሰራት ይገባቸዋል ብለን የምናምንባቸውን በውስጣችን የሚመላለሱ መልካም ሃሳቦችን በጋራ በመምከር የምናምንባቸውን በውስጣችን የሚመላለሱ መልካም ሃሳቦችን በጋራ በመምከር የምንተገብርበት፣ በህይወት ያሉትን መምህሮቻችንንና በኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ ጉልህ አስተዋጽዖ ያበረከቱ ባለሙያዎችን የክብር ዕውቅና የምንሰጥበት፣ በህይወት የሌሉትን ደግሞ የምንዘክርበት፣..." የሚሉ ነበሩ።

ከየግል ኑሯችን የምትተርፈንን ጊዜ እያብቃቃን ለዝግጅቱ መሳካት ጥረት አደረግን። በቅድሚያ ለዝግጅቱ ማከናወኛ የሚሆን ገንዘብ ከየራሳችን ኪስ እንድናወጣ ተወሰነ። ከቁጥራችን ማነስ የተነሳ፣ ጫናው ከፍተኛ መሆኑ ሲታወቅ ደግሞ፣ የሙዚቃ መሣሪያ በእጃችን እያለና መጫወት እየቻልን፣ ለምን የምናውቃቸውን ድምጻዊያን እንዲተባበሩን በመጠየቅ የገቢ ማግኛ ምሽቶችን አንፈጥርም የሚል ሃሳብ ብቅ አለ። እንዲህ አይነቶቹን ሃሳቦች በማፍለቅ የታወቀው የተሻገር ይልማ ሃሳብ ነበር፤ ሃሳቡም ቅቡልነትን አገኘ፤ ወደ ተግባርም ተለወጠ።

በየሁለት ወሩ ልዩነት ሁለትና ሶስት ድምጻዊያንን ለትብብር በመጠየቅ፣ በሁለት ሬስቶራንቶች ተባባሪነት የሙዚቃ ምሽት ዝግጅቶችን አደረግን ።(በዚህ አጋጣሚ-ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ሰውተው ከተለያዩ ስቴቶች ወደ ቬጋስ በመምጣትና ያለምንም ክፍያ በነጻ ለእኛ ዝግጅት መሳካት ከፍተኛ አስተዋጸዖ ላበረከቱልን ድምጻውያን፣ አያሌው መስፍንና አለም ከበደ፣ ንጉሤ ቦጋለና ገነት አባተ፣ ቤዛ ታደሰና ፋሲካ ዲሚትሪ፣ እንዲሁም የከተማችን ነዋሪ ለሆነው ወጣት ሚኪ ዜማ የከበረ ምስጋና ይድረሳቸው!)









ይህ ሁሉ ተደርጎ ቋት ባይሞላም፣ በተገኘው ደገስን። ወደ ዝግጅቱ መዳረሻ ሳምንት ላይም፣ ከውጭ የሚመጡት የያሬድ ምሩቃን እንግዶቻችን ወደ ላስ ቬጋስ መግባት ጀመሩ፤ ዶ/ር እዝራ አባተ (ከኢትዮጵያ)፣ ኃይሉ ካሣዬ (ከጀርመን)፣ ፋንታሁን ሸዋንቆጨው (ከካናዳ)፣ በድሉ ተክለ-ማርያም ከባለቤቱ ከኢሌኒ ጋር( ከሎንዶን)፣ ጥላሁን ሲሣይ (ከጀርመን)፣ በኃይሉ ክፍሌ (ከካናዳ)፣ ከሃገር ውስጥም፣ የክብር እንግዳችን ጋሼ አማኒ ኢብራሂም (ከሜሪ ላንድ)፣ ምስክር ከፍያለው (ከካሊፎርኒያ)፤ ላስ ቬጋስ ካለነው የያሬድ ምሩቃን ጋር ሲደመሩ፣ የቬጋስ ከተማ ወደ አስራ ሰባት የሚሆኑ የያሬድ የሙዚቃ ት/ቤት ምሩቃንን ማስተናገድ ያዘች።



ኦክቶበር 25፣ 2017 ረቡዕ ዕለት ምሽት ላይ በፓላስ ስቴሽን አዳራሽ፣ ያሬዶች፣ ቤተሰቦቻቸውና ጥቂት ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ታደሙ። በቅርቡ ላለፈው መምህራችን ለአቶ ሰሎሞን ሉሉ እንዲሁም አስቀድሞ ላለፉ መምህራን፣ ተማሪዎችና በአጠቃላይ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩን የጥበብ ሰዎቻችን የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት ተደረገ።



ዝግጅቱን በቀልድ እያዋዛ የሚመራው ፋንታሁን ሸዋንቆጨው መድረኩ ላይ ተንጎራደደበት ፣ ታዳሚው በደስታ ሳቅ አወካ...፤ ቬጋሶችን ወክሎ ሰሎሞን አባተ የእንኳን ደህና መጣችሁ አጭር ንግግር አደረገ። መድረኩ በሙዚቀኞችና በመሳሪያዎቻቸው ተሞላ፤ ታምሬ ወልደየሱስ (ቤዝ ጊታር)፣ ረዘነ ሃብቴ(ሊድ ጊታር)፣ ሳምሶን ጁፋር (ድራም)፣ እዝራ አባተ ( ኪ-ቦርድ)፣ ዳዊት አብርሃም (ቴነር ሳክስ)፣ ሰለሞን አባተ (አልቶ ሳክስ)፣ ተሻገር ይልማ (ሳውንድ ሲስተምና ዲጄ)፣ ፋንታሁን ሸዋንቆጨው (ድምጻዊ)።





“...ክበር ተመስገን የኛ ጌታ፣ ...ክራሬን ብቃኘው፣ ..የከርሞ ሰው..” በድምጽና በመሳሪያ ቅንብር ስራዎች አዳራሹ ደመቀ፤ ስለ ያሬድ ሙዚቃ ት/ቤታችን የተዘጋጀው ጽሁፍ በዶ/ር እዝራ አባተ ቀረበ፤ በየመሃሉ የጌትነት እንየው (በነጻ ገበያ) እና የበእምነት መላኩ (በማንነታችን እንድመቅ)ግጥሞች ተነበቡ፤ የያሬድ ትውስታ በግጥምና በመነባንብ ተደመጠ። አዳራሹ በደስታ እንደተሞላ፤ ሳናውቀውና የዕለቱን ዝግጅት ሳንጠግበው ሰዓቱ ተገባደደ። የዕለቱ ዝግጅት ፍፃሜ ሲቃረብ አንድ ነገር ይቀረን ነበር፤ የእለቱን የክብር እንግዳችንን ጋሼ አማኒ ኢብራሂምን ማክበርና መሸለም።





እምናከብረውና እምናደንቀው፣ በመምህርነቱና በጥበብ የፈጠራ ስራዎቹ አማካኝነት፣ መልካም አርዓያነት ያለው አሻራ በተማሪዎቹ ላይ ያሳረፈው የክብር እንግዳችን ጋሼ አማኒ ኢብራሂም፣ በኛ አቆጣጠር ከ1970ቹ ጀምሮ በያሬድ የሙዚቃ ት/ቤት በመምህርነትና በርዕሰ-መምህርነት፣ በባህል ሚ/ር መስሪያ ቤት የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ በአማካሪነትና በሃላፊነት፣ በሀገሪቱ ከፍተኛ የበዓላትና የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ በሙዚቃ ደራሲነት፣ አቀነባባሪነት፣ አዘጋጅነትና መሪነት፣ ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከተ የጥበብ ሰው ነው። እነሆም! ከአያሌ ዓመታት መለያየት በኋላ፣ የቀድሞ ተማሪዎቹ ዳግም ስላገኘነው እጅግ ከፍተኛ ደስታ ተሰማን፤ አከበርነው፤ ሸለምነውም።

በዝግጅታችን ላይ ከተገኙ ተጋባዥ እንግዶች መካከል የታወቁና በስራዎቻቸው የተከበሩም ነበሩ፤ በችሎታው የተደነቀውና አሉ ከሚባሉ ጥቂት ድራመሮቻችን አንዱና ዋናው የሆነው ድንቅ የድራም ተጫዋቹ *ሳምሶን ጁፋር* (ሳሚ)፣ ከዋሊያስ ባንድ መስራቾች አንዱ የነበረውና ከአያሌ የሀገርና የውጭ ሀገር የሙዚቃ ባንዶች ጋር የተጫወተው እውቁ ሊድ ጊታሪስት *ረዘነ ሃብቴ*፣ ለሕዝብ ባበረከተው የላቀ አግልግሎት በየወቅቱ የተለያዩ ሽልማቶች ባለቤት የሆነው፣ ጋዜጠኛና ሁለ-ገብ ባለሙያው የጸሐይ አሳታሚና ኤዲቲንግ ዳይሬክተር ትሁቱ *ኤልያስ ወንድሙ* ይገኙበታል።





ይህ የመገናኛ ዝግጅታችን የተሳካና ያማረ እንዲሆን፣ የአያሌ ወዳጆቻችንና ቤተሰቦቻችን ድጋፍ አልተለየንም። ያገኘነውን ደስታ እንድንጎናጸፍ ካገዙን ጥቂቶቹ፣ ከአበባ ማበርከት እስከ ፎቶ ማንሳት አገልግሎት የሰጠችው ማኅልየ ሰለሞን፣ ዝግጅቱን ሙሉ በፎቶግራፍ የቀረጸው ናቲ፣ እንግዶችን በማመላለስና ቁርስ በመጋበዝ የተባበረው ሐብታም፣ የዝግጅቱን ተሳታፊዎች በሙሉ ወደ መኖሪያ ቤቷ ጠርታ ራት ያበላችው እውቋ የውዝዋዜ ባለሙያ ገነት አፍለይ፣ ወጪዎቻችንን የተጋሩልን፣ አብይ-አቢሲንያ፣ ሜሞ፣ ሉሲ፣ እናት ገበያ፣ ፣ ላዕከ፣ ገብርኤል፣ አብርሃም ሊሞ፣...እንዲሁም በዝግጅቱ ላይ የተሳተፉና ምግብ በየቤታቸው እየሰሩ የጋበዙን ቤተሰቦች ባለውለታዎቻችን ናቸው።











በሁለተኛው ቀን (ኦክቶበር 26፣ 2017)ያሬዶች ብቻችንን ከተምን። በትናንትናው ዝግጅት ሊቀርብ ታስቦ በጊዜ እጥረት ያደረውንና ኃይሉ ካሳዬ ከሃገር ቤት ቀድቶ ያመጣውን፣ ስለጋሼ አማኒ፣ የቀድሞ ተማሪዎቹና የስራ ባልደረባዎቹ ምስክርነት የሰጡበትን አጭር ቪድዮ ተመለከትን። ከሃገር ቤት ብዙ ጊዜ የራቅን፣ በቪድዮው ላይ የምናያቸውንና የምናውቃቸውን እነ ገዛኸኝ ኃይሌ፣ ሰለሞን ሉሉ፣ በቀለ ደብሬ፣ ዓይናለም ወልዴ፣ ፍቅርተ ደሳለኝ፣ አክሊሉ ዘውዴ፣ ኩስያ ጦሎንጌ፣ ወሰንየለህ መብረቁን ስንመለከት ተመሰጥን። ስለ ጋሼ አማኒም የሚያውቁትን የስራ ጥንካሬና ዲሲፕሊንም በስሜት ሲመሰክሩ አደመጥን።

ከምሳ መልስም በተከታዩ ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባን ተወያየን። ከአስራ ስምንት ወራት በኋላ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎችን ጨምሮ ዳግም ለመገናኘትም ወሰንን። በቁምነገሩ ማግስት ዘነበወርቅ ገዛኸኝና ባለቤቷ ሞገድ ጠረጼዛ የሞላ ቁርስ አስተናገዱ፤ ከቁርሱም በኋላ ጨዋታው ደመቀ፣ ሙሉ ቀን ተሳቀ፤ በማያባሩት የፋንታሁን ሸዋንቆጨው ቀልዶችና ያለፉ ትዝታ ወጎች እንባችንን እየጠረግን በሳቅ አወካን፤ የመንፈስ እርካታ እንደ ዓመት ስንቅ ተሸመተ፤ ከባቢው በደስታ ተዋጠ። በነጋታውም ሐብታሙ ቤት ተደገመ፤ ቤተሰብአዊነት ነገሰ...።





የመለያያችን ዕለት ደረሰ፤ የመጨረሻዋንም ምሽት በአበሻ ሬስቶራንት ውስጥ አደመቅናት። በየጨዋታውና ሳቁ መሃል፣ ፋንታሁን ሸዋንቆጨው፣ የጋሼ አማኒን የድሮ መዝሙሮችን አዝማቾች እያዜመ አስታወሰን፤ "...ያራዊቶቿ አይነት፣ ኒያላ ዋልያ፤ ውበት ተፈጥሮዋ ልዩ መመኪያዋ..."፣ የእናት ሀገር ፍቅርን ሲያሰርጹብን የኖሩትን እነዚያን ውብ ህብረ-ዝማሬዎች ስናስታውስ፣ ሩቅ.. ዓመታት ወደኋላ ተመልሰን መዝሙሮቹን ስንዘምር የቆምንባቸውን ቦታዎች ሁሉ እስከምናስታውስ ድረስ በትዝታ የነጎድን ነበርን። ጋሼ አማኒ ለሰጠን ጥንካሬና በራስ የመተማመን መንፈስ አመሰገንነው፤ አርዓያነቱን አከበርነው፣ የተሰማንን ሁሉም ነገርነው፤ በሁላችንም ፊት ላይ የደስታ ፍካት ገጽታ ይነበብ ነበር፤ ጋሼ አማኒም ተደሰተ፤ ለአንድ መምህርና ታላቅ ወንድም ከዚህ በላይ ምንስ ሊያስደስተው ይችላል...?!

የከርሞ ሰዎች ይበለን!

ጌታቸው አበራ
ሕዳር 2010 ዓ/ም
(ኑቬምበር 2017)